Melaku_geleta@hotmail.com

USA

ግልፅ ደብዳቤ ለህወሃት (Open Letter to TPLF)

Ethiopia 360° ! የኢትዮጲያ አከራሞትና ዘለቄታ!!!

Cc: To the people of Tigray region ( የትግራይ ህዝብ )

US Embassy Ethiopia (የአሜሪካ ኤምባሲ)

EU Delegation to Ethiopia (የአውሮፓ ህብረት)

African Union Commission (የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን )

The people representative parliament of Ethiopia (የኢትዮጲያ መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት)

EPRDF member party's (ለኢሃአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋር ድርጅቶች)

UN Human Right Commission Geneva ( በተባበሩት መንግስታት ለሰባዊ ኮሚሽነ )

የሞቱ ተስፋዎች (The dead hops)

ይህንን ንኡስ ርእስ የምጀምረው በሚከተሉት የዝማሬ ሀረጎች ነው፡፡

እንደማያልፍ የለ ያ ! ሁሉ አለፈ

ታጋይ የህዝብ ልጅ በላቡ በደሙ ደማቅ ታሪክ ፃፈ!

ይህ ዝማሬ የተዘመረው ህወሃት መራሹ የትጥቅ ትግል በተገባደደ ማግስት ይመስለኛል፡፡ አንድ ትውልድ ወደ ሌላ ምእራፍ ከተሸጋገረ በሁዋላ ነው፡፡ የ17 አመታት የእርስ በእርስ ጦርነት ከተጠናቀቀ በሁዋላ ህወሃት ወደስልጣን ወጥቶ 27 አመታት ተቆጥረዋል፡፡ በ27 አማታትም ኢትዮጲያ ከጦርነት አላረፈችም፡፡ ልዩነቱ ጦርነቱ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፡ ምስራቅና ምእራብ ተስፋፋ፡፡ የህን ከላይ የጠቀስኩትን ስንኝ የዘማረ ትውልድ አንጋፋዎች ዛሬም በኢትዮጲያ ፖለቲካ ውስጥ መሪና ዋና ተዋናይ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት በስልጣን ላይ የነበሩት ያሚሪካው ጂሚ ካርተር፡ ዶናልድ ሬጋን ፡ ጆርጂ ቡሽ፡ ቢል ክሊንተን ና ባራክ አባማ አንዴ በዲሞክራት ሌላ ጊዜ በሪፓብሊካን ፓርቲዎች ሀገራቸውን እየመሩ መጥተው ሄደዋል፡፡ እንደ ተማረ ኢትዮጲያ ይህንን እያዩ መኖር በጣም ያሳፍራል፡፡ ይህ ዝማሬ በርግጥ ኢትዮጲያን ለማሸጋገር የተዘመረ ዝማሬ ከሆነ ህወሃት ይህንን በመሰለ ጭንቅ ውስጥ ሆኖ ኢትጲያን ለመምራት መቸገር ያለበት አይመስለኝም፡፡ የተከፈለው ዋጋ በርግጥ አትዮጲያን ወደ ዲሞክራሲ ለማሸጋገር ከሆነ ህወሃት ከክብር ስፍራ ይልቅ ለምን የውርደት ስፍራ እንደመረጠ ግር የሚያሰኝ ነው፡፡ አሁን ያለው የህዝብ እንቢታ በምን መልኩ የክብር ምልክት አመስለኝም፡፡ ለትግራይ ሰማዕታት የማይመጥን እብሪት እየተስተዋለ ነው፡፡እኔ ይህንን የምፅፋ የትግራይና የኤርትርያ አብሮ አደግ ጓደኞቼን እያሰብኩ ነው፡፡ 27 አመታት አንሶ ነው ዛሬ የህዝብ ልጆች ባደባባይ በጥይት አረር የሚቀጠፉት፡፡ ምን የሚሉት ልበ ደንዳናነት ነው፡፡ ህዝቡ በተደጋጋሚ ለእልቂት አምርሮ በተነሳበት ሰአታት ሁሉ ጣልቃ ገብተን መማጠናችን ነገሮችን እንደለወጠ ካልተገነዘባችሁ መጪውን ጊዜ ለታሪክና ለህዝቡ መልቀቅ ያለቀ አማራጭ ነው፡፡ ኢትዮጲያን የጋራ ቤት የማድረግ ሃፊነት በዋናነት ሀገርን ከሚመራ ቡድን ወይም መንግስት ይጠበቃል፡፡ሰማዕታት የትግራይ ጀግኖች በደማቸው የፃፍት ደማቅ ታሪክ ይህ ከሆነ የኢትየጲያውያን ታሪክ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ ኢጋዴን ያልታወቀ እልቂት፡ አዋሳ በመቶዎች የሚቆጠሩ፡ ጋምቤላ በመቶዎች የሚቆጠሩ፡ በሺዎች የሚቆጠሩ በአማራ ክልልና በሃገሪቱ በተለያዩ ስፍራዎች አልቀዋል፡፡ ኦሮሞ በስደት፡ በእስር ቤት ብሎም በብዙ ሺዎች ተገለዋል ፡፡ አሁን በዚህ ሰአት ኦሮሞ እየታሰረ፡ እየተገደለ ብሎም ከሀገር እየተሰደደ ነው፡፡ አንድ ሚሊዮን እዝብ የእለት ጉርስ ተመጥዋች የተደረገው “ታጋይ

የህዝብ ልጅ  በላቡ በደሙ ደማቅ ታሪክ  በፃፈባት በኢትጲያ ምድር ነው “ ፡፡ ዛሬ ያንን የደማቅ ታሪክ ባለቤት ፍሊጋ የትግራን ህዝብ በይፋ ለህዋሃት በተፃፈ ደብዳቤ ግልባጭ ለመጠየቅ ተገድጃለሁ፡፡ ያስተማርኳቸው ልጆች ባደባባይ ሲገደሉ፡ ያስተማረኝ ህዝብ በቀየው ሲዋረድ፡ እንግዳ ተቀባዩ ኦሮሞ ውላታ ቢስ ሲደረግ ይህን ከመሞገት ውጭ አማራጭ የለም፡፡

<u>ጉሬዛ ለቆዳዋ ኦሮሞም ለሃብቱ ሞት ተፈረደበት!</u>

ዘረኛ ሄኘ አይደለም  የኦሮሞን ጉዳይ ነጥየ  ለመመልከት የፈለኩት፡፡  መላው ኢትዮጲያ  በችግር ውስጥ ቢሆንም የኦሮሞ ግን የተለየ እንደሆን ማሳየት እፈልጋለሁ፡፡  ከሶስት ቀናት በፊት በትውልድ መንደሬ ተማሪዎች ያደረጉትን ሰላማዊ ተቃውሞ ለተመለከተ 27 አመታት ሙሉ ኦሮሞ የተገደለው ና በእስር የማቀቀው መንግስትን በሃይል ለመለወጥ በሚል አንቀፅ ቢሆንም  እውነቱ ግን ዛሬም ባደባባይ እየተገደለ ም ነቀምት ላይ እንደታየው  ጥያቄው ሰላማዊ ነበር፡፡ የ27 አመታቱን ብንተው ባለፉት 3 አመታት ኦሮሞ ፍዳ ያየው አድፍጦ ሰው በመግደሉ አይደለም፡፡ አብረውት የሚኖሩትን የሌላ ብሄር እዝቦች (ትግራይንም ጨምሮ) በማጥቃቱ አልነበረም፡፡ አንቀፅ 39ን ለመተግበር አልነበረም፡፡ በነፍጥ የታገዘ  ፍልሚ መንግስት ላይ ከፍቶ አልነበረም፡፡በመንግስት መዋቅር ሽፋን የህዝቡ መሬት በጠራራ ፀሐይ በመዘረፉ ነው ፡፡ የህን ዝርፊያ መኖሩን  መንግስትም ያምናል( ጠቅላይ ሚኒስትሩ በይፋ አምነዋል) ፡፡ በዚህ ጥያቄ የተነሳ ዛሬ ድረስ በቀለ ገርባ፡ መረራ ጉዲናና ሌሎች አያሌ ኦሮሞዎች በእስር እየማቀቁ ነው፡፡ ኮሎኔል ደመቀ የእስር ሰለባ የተደረገው በተመሳሳይ የመሬት ጥያቄ ጉዳይ ነው፡፡ ኦሮሞ ያለማንም ጣልቃ ገብነት እራሴን ላስተዳድር በማለቱ ነው እየተገደለ ያለው፡፡ ለሁሉም የሃገሪቱ ህዝቦች የተሰጠው ህገመንግስታዊ መብት ሳይሸራረፍ ለኦሮሞም መከበር አለበት በማለቱ ብቻ የተፈረደባት ሞት ነው፡፡ በምን ስሌት ፍትሃዊ ሊባል ይችላል ከኦሮሞ ላይ በ 70 ብር  የተወሰደ 1 ካሬ ሜትር መሬት በ20 ና 30 ሽህ እየተሸጠ ኦሮሞ ዝም በል የሚባለው፡፡ ሲናገር መገደሉስ ፍትሐዊነት ነው??? ይህ የተደረገው “ታጋይ የህዝብ ልጅ  በላቡ በደሙ ደማቅ ታሪክ በፃፈባት በኢትጲያ ምድር ነው “ በሱዳን ፡ በየመን፡ በሊቢያ ወይም በሶርያ አይደለም፡፡ ቦረናና ጉጂ ውስጥ ፡ ፊንፊኔ ዙሪያ በአምስቱም አቅታጫ  ላይ፡ አርሲ ፡ ወለጋ ፡ ባሌ ፡ ኤሉባቦር የህዝብ ሃብት በብጣሽ ወረቀት ሲዘረፍ ያው ትውልድ   “ታጋይ የህዝብ ልጅ በላቡ በደሙ ደማቅ ታሪክ  በፃፈባት በኢትጲያ ምድር ነው “  ፡፡ ጉዳዩ ትግሬን የመጥላት ተደርጎ መተርጎሙ ደግሞ የበለጠ ያሳምማል፡፡ ምነው ህሊና የሚባል ክቡር ሃብት እዴት ብህዝብ ደረጃ መቀመቅ የገባል??? ሞራልና ፈሪሃ እግዜአብሔር  የሚባል መለያ እንዴት ከሃገር ይጠፋል??? ኦሮሞ  በምንም ሊሳበብ የማይችል መከራ እየተጋተ ያለው ለቆዳዋ እንደተገደለችው ጉሬዛ  መሆኑ ነው፡፡

<u>መንግስት ተንኮል ይከላከላል ብቻ ሳይሆን  አይሰራምም!</u>

አሁን በምስራቁና በደቡቡ የኢትዮጲያ  ክፍል  የተፈጠረው ሰው ሰራሽ ግጭት በዚህ ደረጃ መከሰቱ መንግስት ምን እየሰራ ነው ብለን ለመጠየቅ በሶማሌና በኦሮሞ መካከል ግጭት እንዳልነበረ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ በዋናነት አርብቶ አደሩ ኦሮሞ ይጋጭ የነበረው ከገሪ፡ገብራ፡ መሪሃንና  ሀዊያ  ንኡሳና ጎሳዎች ጋር ነው፡፡ ገሪና ገብራ ደግሞ ሲፈልጉ ኦሮሞ ሲፈልጉ ደግሞ እራሳቸውን ሶማሌ ብለው የመለዋወጥ ዝንባሌ አላቸው፡፡ የወቅቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ አኗኗራቸውን ይለዋውጠዋል፡፡ የሁለቱንም ቋንቋና ባኅል በሚገባባ ያውቃሉ፡፡ እዚያ ሁለት ክልል የሚፈጠረውን ግጭት ከተባባሰ እነዚህ ወገኖች መጠቀሚያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ የዘንድሮው ግን የተለየ የሆነው በመንግስት የሚደገፍ ሃይል በሁሉም ደረጃ መሳተፉ ነው፡፡ ጦሱ የተረፈው ለኦሮሚያ ክልል መንግስት፡ ለኦሮሞ ህዝብ ሆኖ ሲታይ ይህ ህዝብ ለምን በዚህ ደረጃ ጥቃት ይከፈትበታል የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ እውነት የኦሮሞ ህዝብ ለኢትዮጲያ ባለውላታ አይደለም??? የሚል ጥያቄ ያጭራል፡፡ 600፣000 ህዝብ ከመሰረታዊ ኑሮው ተፈናቅሎ ህዝቡ ያመራው ወደጦርነት ሣይሆን ህዝቡን መልሶ ወደማቋቋም ነበር፡፡ ለመሆኑ ምን ነበር የተፈለገው ??? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ህዝባዊ መተላለቅ ??? ይህ መንግስትን የሚያስደስት ከሆነ በርግጥም ያልተነገረን የበቀል ጦር ወይም ሰይፍ በምድሪቱ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለትውልድ የሚተርፍ ጠባሳ ላለመተው መተማመኛ የለንም፡፡

<u>በአሁኑ የኢትዮጲያ ሁኔታ የለውጥ አቀንቃኙ ማነው? መአህድ፡ ሰማያዊ ፓርቲ፡ ኦፌኮ ፡ መድረክ፡ አነግ፡ግንቦት7 ፤ ኦህዴድ ብአዴን ወይስ ሌላ፡፡</u>

የፖለቲካ ግለቱ ከክልል ክልል ቢለያይም በጥቅሉ በኢትዮጲያ በመንግስት ላይ እተደረገ ያለው ግፊት እመጣ ያለው (ከትግራይ በስተቀር) ከህዝቡ ነው፡፡ እነዳለመታደል ሆኖ   “ታጋይ የህዝብ ልጅ በላቡ በደሙ ደማቅ ታሪክ  ፃፈ “ ተብሎ የተዘመረው ዝማሬ በንፁኃን የህዝብ ልጆች ደም ሊጨቀይ ጥቂት ሳምንታት ብቻ ነው የቀሩት፡፡የካሁን በፊቱን በምህረት የማለፍ በሳልነት ከህዝቡ ከተገኘ ለማለት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ተኩኖ አሁንም ሌላ ሃሳበግትርነት ይታያል፡፡ ምን ተፈልጎ ነው፡፡ ታላቁ መፅኃፍ ቅዱስ “ ትእቢት ውድቀትን ትቀድማለች" ይላል፡፡ ወዴት እያመራን ነው እየተባለ ሲጠየቅ ሁለት አስርት አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ዛሬ የደረስንበት ስፍራ ግን ከበፊቱ  የተለየ ነው፡፡ ዛሬ ሰላሮሞ ህዝብ ሸንጡን ገትሮ በመሞገት ላይ ያለው ታሳሪው በቀላገርባ ወጣቱ ለማ መገርሳ  ወዘተ ናቸው፡፡ ሽማግሌው ገላሳ ዲልቦ፡ ፤ አብዩ ገለታ፡ ሌንጮ ለታ፡ ቡልቻ ደመቅሳ ወይም ደውድ ኢብሳ አይደሉም፡፡ የለማንም ሆነ የበቀለን ትግልና የትግል ስልት ከቀደሙት የኦሮሞ ታጋዮች ጋር ማሳከር ተቀባይነት እያጣ ነው፡፡  በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ብሎም ለታሪክ በሚተው ምክንያት በኦሮሞና በሌሎች ህዝቦች መካከል እነዲፈጠር የተደረገው ግድግዳ በዚሁ ትውልድ በዚሁ መንግስት

አደባባይ እንደ በርሊን ግንብ፡ እነደ ጎርባቾቭ ትሮይስካ ብትንትኑ እየወጣ ነው፡፡ ይህ ለመጪው ጊዜ ተስፋ ቢሆንም የዛሬውን ጨለማ ለማለፍ ትውልዱ የተተያያዘውን ቅዱስና ዘመኑን የዋጀ ጥያቄ ዘመኑን የዋጀ ምላሽ መንፈግ ህገሪቱም ሆነች በዋናነት የኦሮሞ ሕዝብ የሚከፍለውን ዋጋ ውድ እደረገው ነው፡፡ እራሱን ለመስዋእት ካቀረበ ትውልድ ጋር ከልኩ ያለፈ እልክ መግባት የጥፋቱን መጠን አሳዛኝም አስከፊም ብሎም የታሪክ ጠባሳ የሚተው ያደርገዋል፡፡

<u>የህዝቡን ጥያቄ ባግባቡ አለመመለስ የጥፋት አማራጮችን ይጋብዛል!</u>

ኢትዮጲያም ሆነች የአፍሪካ ቀንድ አንድ በግልጽ ያልወጣ አደጋ ለማስተናገድ በዝግጂት ላይ ናቸው (latent Disaster) የሂደቱን ትንታኔ (trend analysis) በሌላ ጊዜ እንመለሰበታለን፡፡ ከሁሉም ደግሞ ይህ አሁን ኢትዮጲያ ከምትገኝበ ታሪካዊ ወቅት አንጣር የሀገሪቱን አንድነት በእጅጉ እንደሚጎዳ ሀገር ለሚመራ መንግስት ሊሰወርበት አይገባም፡፡ በቅርቡ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪቤት ቅርብ የሆኑት ሀርማነ ኮሆን Herman Cohen ተገቢውን ምክር ለግሰዋል ፡፡ ብሄራዊ እርቅ ብቻ ነው ኢትዮጲያን የሚያተርፋት national reconciliation ብለዋል፡፡ ህዝቡ መገዳደል ይጀምር ዘንድ መንግስት ከፈቀደ ያሳዝናል፡፡ ሳቃጠል በቅጠል ማለት ነው፡፡ ታሪካዊ ሃላፊነት በህወሃት ላይ እንዳለ ሳማሳሰብ ነው አድራሻውን ለህወሃት ያልኩት፡፡ በግልባጭ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ ማለቴ የትግራይ ህዝብም ህወሃትን ወደ ተቀደሰ ታሪካዊ መንገድ ይመራ ዘንድ በመተማመን ነው፡፡ ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ ማለት በዚህ ሰፍራ ያስፈልጋል፡፡

Ethiopia 360° ! የኢትዮጲያ አከራሞትና ዘለቄታ ይቀጥላል !

December 15, 2017

እባካችሁ ይህን ፅኁፍ ለሚመለከታቸው ሁሉ በማካፈል ግዴታችሁን ተወጡ፡፡